በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ...

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

የካቲት ፲፩ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ…

## መግቢያ

- ክርስቲያናዊ ትዳር ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ በእግዚአብሔር እንደተሰጣቸው ለሚያምኑ ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው፡፡
- ምስጢረ ተክሊል ከሰባቱ የቤተ ክርስቲያናችን ምስጢራት አንዱ ሲሆን ተጋቢዎቹ አንድ ወንድና አንዲት ሴትን በቤተ ክርስቲያን በሚፈጸምላቸው ሥርዓትና ጸሎት በእግዚአብሔር አንድ ያደርጋቸዋል፡፡
- ተጋቢዎቹም ይህን ሲገነዘቡ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በሆኑት ሁሉ ደስ እየተሰኙ ሰማያዊ ሕይወትን በምድር ላይ በፍቅር፣ በደስታ፣ በሰላምና በጽድቅ መምራት ይቻላቸዋል፡፡
- በክርስቶስ እግዚአብሔር የሆነ ጋብቻ ሳይበጠስ ለዕድሜ ልክ ተጠብቆ የሚኖር ትስስርና ቃል ኪዳን ነው፡፡
- ይህም መተሳሰር ወይም አንድነት በክርስቶስ አማካይነት ተጋቢዎቹን በማይቋረጥ መንፈሳዊ ሕይወትና መተባበር ያኖራቸዋል፡፡
- በክርስቶስ የሆነ ጋብቻ ተጋቢዎቹ ከትዕቢት፣ ከትምክህት፣ ከራስ ወዳድነት፣ ከስግብግብነት፣ ከኢፍትሐዊነት ጋር ተዛምዶ ያላቸውን መጥፎ አመለካከቶች እያስወገዱ ወደ ሰማያዊው መንግሥት የሚገቡበት ጠባብ በር ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ…

## መግቢያ

- በክርስቶስ የሆነ ጋብቻ ክርስቲያናዊ ሀብታትን የምንላበስበትና ስለ ትዕግሥት፣ መከባበር፣ ጸጥተኛነት፣ ራስን መካድ፣ ርኅራኄ፣ ታማኝነት፣ ማስተዋል፣ ጥበብና ይቅርታ ለመማር ዕድል የምናገኝበት ትምህርት ቤት ነው፡፡
- በክርስቶስ የሆነ ጋብቻ ‹‹በክርስቶስ ካልሆነው›› ጋብቻ ፈጽሞ ይለያል፡፡
- ጋብቻቸውን በክርስቶስ ሆነው የሚመሠርቱ ፍጻሜ በሌለው የፍቅር፣ የጸጋና የበረከት ውቅያኖስ ውስጥ ይዋኛሉ፡፡
- በክርስቶስ ሳይሆኑ ጋብቻቸውን የሚመሠርቱ ግን ውጤት በሌለው ትግል ውስጥ ወድቀው በጭንቀት፣ በፍርሐት፣ የሥጋ ምኞትና ጥላቻ ተዘፍቀው ሲንገላቱ ሲዳክሩ ይኖራሉ፡፡
- በክርስቶስ ከሆነ ጋብቻ የሚገኙ ልጆች ከጋብቻው በረከት የሚካፈሉበትና ይህን ወደሚመስልም ሕይወት አድገው የነገዎቹ ሙሽራና ሙሽሪት ለመሆን የሚበቁበት ዕድል ያገኛሉ
- እንግዲህ በክርስቶስ የተጀመረው ጋብቻ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የሚታፈሱበት ባለትዳሮቹም ደስ እየተሰኘን ሰማያዊ ሕይወትን በምድር ሳሉም በፍቅር፣ በደስታ፣ በሰላምና በጽድቅ ተላብሰን እንድንገኝ መላ ሕይወታችንን በሚከተለው መንገድ የምንመራ መሆን ይገባናል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ጠባይ ወይም አመል

## ጠባይ ወይም አመል

- በትዳር ለሚገኝ ደስታ የመጀመሪያው ቁልፍ ነገር የተጋቢዎቹ አመል ወይም ጠባይ ነው፡፡
- ጠባያችን ወይም አመላችን አንዱ ሌላውንም ሆነ ራሱን በሚመለከትበት ሁኔታ እና ባልና ሚስት በአንድነት የገዛ ሕይወታቸውንና በዙሪያቸው የሚገኙ ሰዎችን በሚመለከቱበት ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡
- ለራሳችንም ሆነ ለትዳር አጋራችን ብሎም ባለትዳሮች ሁሉ እርስ በርሳችን ሊያቀራርብ የሚችል መልካም ጠባይን ወይም አመልን መገንባት በትዳራችን ውጤታማ ለመሆን የሚያበቃን ቁልፍ ነው፡፡
- ባል ሚስቱን እግዚአብሔር ለግሉ አድርጎ የሰጣት የሕይወት አጋሩ እንደሆነች ሲገነዘብ ጠባይና አመሉ ሁሉ ምስጋና፣ ፍቅር፣ ክብካቤና መቀበልን ሳይጠብቅ መስጠት የበረከተበት ይሆናል፡፡
- ነገር ግን ተፎካካሪውና ተቃራኒው ወይም ለፍላጎቱ መሟላትና ለጥያቄዎቹ መልስ እንድትሰጠው የተቀመጠች አድርጎ ከቆጠራት ግን ጠባይና አመሉ ሁሉ ትዕቢት፣ ኃይለኝነት፣ ነውጠኛነትና ጥላቻም የሠለጠነበት ወይም የበረከተበት ይሆናል፡፡
- ሚስትም ታላቁን የፍቅርና የመሥዋዕትነት ጉልበትዋን ለባልዋና ለቤተሰቡ ሁሉ እንድታፈስ ለባልዋ የተሰጠች ስጦታ መሆንዋን ስትረዳ ጠባይና አመልዋ ሁሉ ፍቅር፣ ራስን መስጠት፣ መረዳዳትና መሥዋዕትነት የነገሰበት ይሆናል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ጠባይ ወይም አመል

## ጠባይ ወይም አመል

- ነገር ግን ባልዋ መመሪያ ሊሰጣትና እርሱንና ቤተሰቡንም ሁሉ እንድታገለግል የሚያደርጋት አድርጋ ከቆጠረች ጠባይና አመልዋ ሁሉ ጥላቻና ተቃራኒነት የነገሰበት ይሆንና ይህም ወደ አመጸኝነትና ነውጠኝነት ሲያድግ ይገኛል፡፡
- ባልና ሚስት እግዚአብሔር በሕይወታቸው ያዘጋጀውን ዓላማ እንዲፈጽሙ ያዘጋጃቸው የእግዚአብሔር ልጆች አድርገው ራሳቸውን ከቆጠሩ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርባቸው የሚችለውን ጠባይ ይገነባሉ በዚህም አካሄዳቸው እርስ በርሳቸው ተቀራርበው ደስታ፣ ሰላምና እርካታ የሞላበትን ሕይወት ለመምራት የሚያስችለውን ሀብት (ስጦታ) ከእግዚአብሔር ያገኛሉ፡፡
- ባልና ሚስት ገንዘብን ወይም ቁሳዊ ሀብትና ንብረትን ከሁሉ የበለጠ ዋጋ ያለው አድርገው ከቆጠሩ እርስ በርስም፣ ለሰዎችም ሆነ ለሁኔታዎች ያላቸው ጠባይና አመለካከት ሁሉ ራስ ወዳድነት፣ ብቸኝነት፣ ጥላቻ ወዘተ የሞላበት ይሆናል፡፡
- ነገር ግን ኑሮአቸውንና ትዳራቸውን እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች ሁሉ ያለውን ፍቅር ያሳየበት አድርገው ከቆጠሩ ጠባይና አመላቸው ሁሉ ጌታችንን የበለጠ ለማወቅ ያስችላቸው ዘንድ ሁሉን ለማገልገል፣ በዙሪያቸው የሚገኙትን ሁሉ በመርዳት ይታነጽና ቤታቸው የእግዚአብሔርና የክርስቲያኖች ቤት ይሆንላቸዋል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ጠባይ ወይም አመል

## ጠባይ ወይም አመል

- ስለዚህ ከሁሉ አስቀድሞ ከፊታችን የሚገጥመንን የትዳር ፈተና በመቋቋም ደስተኛና የተሟላ ሕይወት ለመምራት የሚያበቃንን መልካም ጠባይ ለመገንባት እንችል ዘንድ ሐሳባችንን፣ ርእያችንን፣ እሴቶቻችንን መገምገም ያስፈልገናል፡፡
- ሌላው ‹‹አመል ወይም ጠባይ›› ተላላፊ መሆኑን ማስታወስ ይገባናል፡፡ የትዳር አጋራችን አመል ወይም ጠባይ ጤናማ ካልሆነ ይልቁንም መጥፎ ከሆነ ፍጹም ትጋት ባለበት ጸሎትና ቀናነትን፣ ትዕግሥትንና ፍቅርንና ፈገግታን በተላበሰ ጠባይ ልናስተካክለው እንችላለን፡፡
- ጤናማ ያልሆነ ጠባይ ያላትን የትዳር አጋር በተመሳሳይ ጤናማ ያልሆነ አካሄድ የምናሸንፍ ወይም የምናስተካክለ አይምሰለን!!! ይልቁኑ ነገሮችን የተሻለ ለማድረግ የሚያስችሉንን እድሎችና ውስጣዊ ሰላማችንን በሙሉ በማሳጣት ***‹‹ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ፡፡›› <u>ሮሜ 12፡21፡፡</u>***ካለን ከጌታችን ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለንን ግኑኝነት እናበላሻለን፡፡
- እንግዲህ እስካሁን በዚህ ጉዳይ ራሳችንን መመልከት ካልጀመርን በሕይወታችን የያዝነውን ለትዳር አጋራችንን የምናሳየውን ጠባይ ወይም አመል ሳይመሽብን ፈጥነን እናስተካክል፡፡
- በርካታ ሰዎች እንዲህ ያለውን ስለትዳር አጋሮቻቸው መልካም አመለካከትን የሚያዳብሩበትን መልካም አጋጣሚ ሳይጠቀሙበት ቀርተው ወይም አበላሽተው የትዳር አጋሮቻቸው በሞት ወደ እግዚአብሔር ከተወሰዱ በኋላ ቁጭትን ብቻ እንዳያተርፉ እንፈራለን!!!

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ድንበር ወይም ገደብ ማበጀት

## ድንበር ወይም ገደብ ማበጀት

- በክርስቶስ የሆነ ትዳራችን ዋስትናው የተጠበቀ እንዲሆን ከትዳሩ ውጪ ካሉት አካላት ወይም ዓለም ጋር ላለን ግኑኝነት ገደብ ማበጀት ያስፈልጋል።
- ከቤተሰቦቻቸው፣ ከአማቾቻቸው፣ ከባልንጀሮቻቸው፣ ከሥራ ጓደኞቻቸው ይልቁንም እርስ በርስም ሳይቀር ተገቢውን ገደብ ማበጀት ስለተሳናቸው የብዙዎች ትዳር በችግር ውስጥ ተዘፍቋል።
- ባልና ሚስት ምንም ዓይነት ገደብ የማናስቀምጥበት ብቸኛው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በተረፈ ግን ራሳችንን እንደ አንድ ቆጥረን ከማንኛውም ሰው ወይም አካል የሚመጣ ጫና ጥሶ እንዳይገባ መጠንቀቅ ራስን መጠበቅ ያስፈልገናል።
- ይህም ማለት ከዓለሙ ሁሉ ጋር ያለንን ግኑኝነት ቆርጠን በመጣል በብቸኝነት እንኑር ማለት አይደለም። የምንለው ከማንኛውም ሰው ጋር ያለ ግኑኝነት በትዳር ሕይወታችን ላይ ጫና ወይም ክፍተት እንዳይፈጥር እንጠንቀቅ ነው።
- ጌታችን አምላካችን ‹‹ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?›› *ማቴ 19፡5።* በማለት የነገረን ቤተክርስቲያን በየጊዜው የምታስታውሰን ለዚሁ ነው። ‹‹ልጄ ሆይ፥ ስሚ እዩ ጆሮሽንም አዘንብዪ ወገንሽን ያባትሽንም ቤት እርሺ።›› *መዝ 44(45)፡10።* ወርቁ ሳይሆን ሰሙ ይህንኑ ያሳስባል።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ድንበር ወይም ገደብ ማበጀት

## ድንበር ወይም ገደብ ማበጀት

- እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ ቤተሰቦቻችንና የቅርብ ወላጆቻችንን አስመልክቶ ይህን ምክር ከሰጠን እኛም ለሌላው ሰው ማድረግ ያለብንም ይህንኑ ነው፡፡
- ነገር ግን ‹‹አባቱንና እናቱን ይተዋል…›› ወይም ‹‹…ያባትሽንም ቤት እርሺ፡፡››  ማለት ምን ማለት ነው? የዚህ ትርጉሙም ከጋብቻ በፊት ከነበርንበት ግኑኝነት መለየት/መሻገር ነው፡፡
- መንፈስ ቅዱስ ‹‹አባቱንና እናቱን ይተዋል ‹‹ከሚስቱም ጋር ይተባበራል - አንድ ይሆናል›› በማለት የገለጠው ባል ከሚስቱ ጋር ያለው ግኑኝነት ከማግባቱ በፊት ከተወለደበት ቀን አንስቶ ከአባትና ከእናቱ ጋር ከነበረው መላ የሕይወት ጥብቅ ግኑኝነት እኩል መሆኑን የሚያስረዳ እውነት መሆኑን መገንዘብ ምንኛ ድንቅ ነው!!! አሁን በጋብቻ የተመሠረተ አዲስ መተሳሰብ ወይም መጣበቅ አለ እርሱም ለዕድሜ ልክ ነው አለን!!!

<u>መለየት/መሻገር</u>

- መለየት ወይም መሻገር የሚለው ቃል የእናቱን ጡት ሲጠባ የነበረ ሕፃን የእናት ጡት ጣለ እንደማለት ነው፡፡ ይህም በተወሰነ መጠን ራስን የመቻልን መንፈስ ስለሚያንጸባርቅ ነጻነትን ይመለከታል፡፡
- ይህም ቀላል ሂደት ወይም ክንዋኔ አይደለም፡፡ በተለይ በቆመበት ሰሞን ለልጁ ብቻ ሳይሆን ከልጅዋ ጋር መገናኘትና በፊት እንደሚያደርገው ልጅዋ በርስዋ መደገፉን እንደተወ ለምታስብ እናትም ከባድ ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ድንበር ወይም ገደብ ማበጀት

## መለየት/መሻገር

- መለየት ወይም መሻገር ሕፃኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሙዓለ ሕፃናት ወይም ትምህርት ቤት ሲገባም ይከሰታል፡፡
- ሕፃኑ/ንዋ ያለ ወላጆች ለረጅም ሰዓት መቆየቱን/ትዋን ሲያውቅ/ታውቅ አምርረው ያለቅሳሉ፡፡
- በተመሳሳይ መንገድም ወንድ/ሴት በጋብቻ ለመኖር ሲተሳሰሩ ሌላ ዓይነት መለየት/መሻገር ይከሰታል፡፡
- በባሕላችን አንዳንድ እናቶች ልጆቻቸውን ጡት ለማስጣል ወይም ከጡት ለመለየት ፈጥነው ፈቃደኛ ስለማይሆኑ  እስከ 2 ዓመት ይዘገያል፡፡ ይህም ምናልባት የሕፃናቱን ዕድገት ዝግተኛ ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ ራሳቸውን ለመቻል ማንነታቸውን ለመገንባት በሚያደርጉትም ቀጣይ ጥረትም የሥነ ልቦና ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይህ ጉዳትም እያደገ ሄዶ ግድ የለሽነትንና ኃላፊነት የማይሰማቸው ሆነው ማደግን ሊያላብስ ይችላል፡፡
- በተመሳሳይ መንገድ ባልና ሚስትም በጊዜው ከወላጆቻቸው ካልተለዩ ራሱን የቻለ ብስለትና ጥንካሬ ያለው ጤናማ የትዳር ሕይወትን ፈጽመው እንዳይቀምሱ ሊያደርሳቸው ይችላል፡፡
- መለየት እንደሌላው ተመሳሳይ አጋጣሚ በመጀመሪያ ሊከብድ ብሎም የሚጎዳ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ለተጋቢዎቹ የተናጠልም ሆነ የጋራ ሕይወት ዕድገትና ብስለት መለየት/መሻገር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡
- ባልና ሚስት ከተጋቡበት ቀን አንስቶ ራሳቸውን ችለው ለመኖር ሲሞክሩ የሚገጥማቸውን ፈተና አውቀው የመጋፈጥን አስፈላጊነት በመረዳት መዘጋጀት የሚያስፈልጋቸውም ለዚህ ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ድንበር ወይም ገደብ ማበጀት

## ድንበር ወይም ገደብ ማበጀት

- ገደብ ወይም ድንበር ማበጀት ማለት በባልና በሚስት መካከል ያለ ግኑኝነት ከንስሐ አባት ወይም ብቃቱ ካለው መካሪ ምክር ተፈልጎ ካልሆነ በስተቀር  እንዳይደፈር አድርጎ የትዳሩን ደኅንነት መጠበቅ ማለት ነው፡፡ የተጋቢዎችም ሕይወት የወላጆች፣ የቤተሰብ አካላት ወይም የጓደኞችና የሌሎችም የቅርብ ሰዎች የወሬ ርዕስ ሊሆን አይገባውም ማለት ነው፡፡
- በርካታ ወላጆች በልጆቻቸው ትዳር የሚያሳዩት ጣልቃ ገብነት ወይም የሚሰጡት አስተያየት የሚያስከትለውን አደጋ ከባድነት አለመረዳታቸው እንደ መጥፎ ዕድል የሚቆጠር ነው፡፡
- የትዳር ሕይወታቸውን ለመጠበቅ የሚያስቀምጡትን ገደብ ወይም ድንበር አስመልክቶም አንዳንድ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ አለመታመናቸውንና ግድየለሽነታቸውን በመግለጽ ቅሬታ የሚያሰሙበት አድርገው በመጠቀም ገደብ ወይም ድንበር እንዳይኖር ለማድረግ ይሞክራሉ፡፡
- በርካታ ባልና ሚስቶችም የትዳር ኃላፊነታቸውንና ተግባራቸውን በመዘንጋት ወላጆቻቸውን ወደሚያስደስት ስሜት ብቻ አዘንብለው የጥፋተኝነት ስሜት ወጥመድ ውስጥ ተጠልፈው በመግባት እንደሚማቅቁ መረዳትም ሌላው መልካም ያልሆነ ዕድል ነው፡፡
- ስለዚህ ለወላጆቻችን በምናሳየው ታማኝነትና ለትዳራችን ስኬታማነትና ዕድገት ባለን ኃላፊነት መካከል ትክክለኛ ሚዛን እንዲኖረን እንደሚያስፈልግ በአግባብ መረዳት ይገባል፡፡
- አባት ወይም እናታችንንን መቼ/እንዴት በትሕትና ሆነን ‹‹አይሆንም›› ልንላቸው እንደምንችልና ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይም ከትዳር አጋራችን ጋር ያለው አዲሱ ግኑኝነት እንደሆነና ከሁሉም በላይ የሆነውን ቅድሚያውን የሚወስደውም ‹‹አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል›› ያለ እግዚአብሔር እንደሆነ ማወቅ እጅግ አስፈላጊያችን ነው፡፡

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
[kesisolomon4@gmail.com](mailto:kesisolomon4@gmail.com)

To get all the lessons, surf :
[www.zeorthodox.org](http://www.zeorthodox.org)